ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

NALA

Sightsavers

የሥነ-ንፅህና ጀግኖች

ፈታኝ ጨዋታ

እያንዳንዱን ፈተና ከጨረሱ በኋላ የእያንዳንዱን ተማሪ ስም በመፃፍ ነጥቦቻቸውን ይመዝግቡ፡፡ ከ 10 ፈተናዎች በኋላ ብዙ ነጥቦችን ያስመዘገበው ተማሪ የሥነ-ንፅህና ጀግና ነው!

ለፈተናዎች የተዘጋጁ ነጥቦች 1-10

ስም	1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	ድምር

ፈተና 1፡ 10 ነጥቦች

ለ 10 ፈታኝ ቀናት ተማሪዎች የእጆቻቸውን እና የፊታቸውን ንጽህና በመጠበቅ ወደ ትምህርት ቤት ይምጡ፡፡ አስተባባሪው ንፅህናቸውን በማረጋገጥ ለእያንዳንዱ ንፅህና ቀን 1 ነጥብ ይሰጣል ፡፡

ፈተና 2: 5 ነጥቦች

ቃላትን ሳይጠቀሙ ትራኮማን ለመከላከል የንፅህና አጠባበቅ ባህሪያትን ያሳዩ!

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

ይሄንኑ መልዕክት በዳንስ ያሳዩ!

ፈተና 3: 5 ነጥቦች

ስለ እጅ መታጠብ እና ስለ ፊት መታጠብ መዝሙር ያዘጋጁ እና ለቡድኑ ይዘምሩ ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

በባንዲራ መስቀል ስነ-ስርዓት ላይ የተዘጋጀውን መዝሙር አብረው ይዘምሩ!

ፈተና 4፡ 5 ነጥቦች

ወደ ትምህርት ቤቱ መፀዳጃ ቤት በመሄድ ውሃ እና ሳሙና መኖሩን ያረጋግጡ ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

የትምህርት ቤቱን ንፅህና እና ጽዳት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ከክለቡ ጋር ይወያዩ፡፡

ፈተና 5: 5 ነጥቦች

ሰዎች ፊታቸውን እንዲታጠቡ ለማበረታታት ሰንደቅ/መልዕክት የሚያስተላልፉ ማስታወቂያዎች ያዘጋጁ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

ሰንደቆቹ/መልዕክት የሚያስተላልፉ ማስታወቂያዎቹንከመፀዳጃ ቤቶቹ አጠገብ ይለጠፉ!

ፈተና 6: 5 ነጥቦች

ስለ ትራኮማ ለቤተሰቦቻቸው ይንገሩ ፡፡

ጉርሻ: 5 ተጨማሪ ነጥቦች

በውሃ እና በሳሙና ፊትን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው ያሳዩ፡፡

ፈተና 7፡ 5 ነጥቦች

በክፍል ውስጥ ላሉት ተማሪዎች የእጅ አስተጣጠብን ያሳዩ ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

የእጅ አስተጣጠቡን በዕድሜ አነስ ላሉ ተማሪዎች ያሳዩ!

ፈተና 8፡ 5 ነጥቦች

ስለ ትራኮማ ድራማ ለማዘጋጀት ከጓደኞቻቸው ጋር ይስሩ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

በእረፍት ጊዜ ለሌሎች ተማሪዎች ያሳዩ!

ፈተና 9፡ 5 ነጥቦች

በእረፍት ጊዜ ስለ ትራኮማ እና እንዴት ትራኮማን መከላከል እንደሚችል ለ5 (የክበብ አባል ላልሆኑ)ተማሪዎች ይናገሩ ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

ለ 5 ተጨማሪ ተማሪዎች ይንገሩ!

ፈተና 10፡ 5 ነጥቦች

የትምህርት ቤቱን ግቢ ከቆሻሻ ለማፅዳት የጽዳት ዘመቻ ያዘጋጁ፡፡

ጉርሻ: ተጨማሪ 5 ነጥቦች

ከጽዳት ዘመቻ በኋላ እጆቻቸውን በውሃ እና በሳሙና ይታጠቡ!